# በሴቶች ሕፃናትና ወጣቶች መብት ዙሪያ በፌደራል ደረጃ ያሉ የሕግ ማዕቀፎች

1. ሴቶችና ህጻናት ለጥቃት ተጋላጭ በመሆናቸው፣ በማህበረሰቡ ከሚሰጣቸው ዝቅተኛ ስፍ፣ ባህልና ሌሎች

ምክንያቶች የተነሳ የተለያዩ ጥቃቶችና ወንጀሎች ሰለባ ናቸው። ይህንንም ከግምት ውስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ መንግስት ከሕገ መንግስቱ አንስቶ የተለያዩ ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስምምነቶች በመፈረም እንድሁም በርካታ አገራዊ ሕጎችን በማሻሻልና በማውጣት አበረታች የሆኑ እንቅስቃሴዎችን ሲያካሂድ ቆይቷል። ከዚህም በተጨማሪ ሕጎችን ለማስፈጸም አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ አደረጃጀቶች ተዘርግተዋል። ሆኖም በአፈፃፀም ደረጃ የሚሰተዋሉ ችግሮች አሁንም አሉ። እንዚህን ችግሮች ለመፍታት ደግሞ በአቅም ግንባታ፣ ግንዛቤ በመፍጠርና የቅንጅት ስራዎችን በማከናውን ስራዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል።

2. ከዚህ ሁሉ በላይ ግን መንግስት አስተዳደራዊ አቅሙን እየተጠቀመ ዜጎቹን የመጠበቅ ኃላፊነት ያለበት እንደመሆኑ በተለይ በትምህርት ቤት ዙሪያ በሚታዩ መጠጥ ቤቶች፣ የሺሻ ቤቶች፣ በመረጃ መረብ በሚሰራጩ ፀያፍ ወይም የብልግና ወይም ለመልካም ፀባይ ተቃራኒ የሆኑ ፊልሞችና ምስሎች (Pornography) እንዲሁም ሌሎች በማህበረሰቡ ውስጥ እየተሰፋፉ የመጡ በሴቶችና ሕጻናትላይ ያነጣጠሩ ችግች ተለይተው አስተዳደራዊ እርምጃዎችን የመውሰድ እንቅስቃሴ መጠናከር አለበት።